ይህ ተማሪ-በተማሪ ላይ የሚፈጥረውን ፆታዊ የሆነ መጥፎ-ባህሪይ መከልከል እና መፍትሄ የመስጠት ፖሊሲ፣ ከዚህ ቀደም በዚህ-ጉዳይ ላይ፣ በDCPS ታውጆ የነበረውን ሁሉንም ፖሊሲ፣ ሜሞራንዳ (memoranda)፣ እና/ወይም መመሪያ የሚሰርዝ እና የሚተካ ነው።

**ቻንስለሩ ያጸደቁት: በስራ ላይ** ______________ ____
**የዋለበት ቀን:** ኦክቶበር (October) 1 ቀን 2021

DISTRICT OF COLUMBIA PUBLIC SCHOOLS

# ተማሪ-በተማሪ ላይ የሚፈጥረውን ፆታዊ የሆነ መጥፎ-ባህሪይን መከላከል እና መፍትሄ-መስጠት

## I. ዓላማ እና የስፋት-መጠን

የኮሎምቢያ ዲስትሪክት የሕዝብ ትምህርት ቤቶች፣ ፆታዊ-የሆነ መጥፎ-ባህሪይን ለመከላከል - ወሲባዊ ትንኮሳ (Sexual harassment)፣ ወሲባዊ ጥቃት (Sexual assault)፣ እና በፍቅር-ጓደኝነት ጊዜ (Dating) ጥቃትን ጨምሮ፤ ደህንነቱ-የተጠበቀ እና ሁሉንም ተቀባይ የሆነ የመማሪ አካባቢን፣ ለሁሉም ተማሪዎች መኖሩን ለማረጋገጥ በቁርጠኝነት ይሠራል። DCPS፣ ተማሪ-በተማሪ ላይ የሚፈጥረውን ፆታዊ-የሆነ መጥፎ-ባህሪይን በጥብቅ ይከለክላል። ይህ ፖሊሲ፣ ስለ - የተማሪ-በተማሪ ላይ የሚፈጥረውን ፆታዊ ትኮሳን፣ ፆታዊ ጥቃት፣ እና በበፍቅር-ጓደኝነት ጊዜ (Dating) ጥቃትን በተመለከተ፣ በስራ-ላይ በሚውለው ሕግ ላይ እንደተገለጸው - እንዲሁም በ2018 የትምህርት ቤት የደህንነት-ጥበቃ ኦምኒባስ (Omnibus) ማስተካከያ ድንጋጌ (የትምህርት ቤት የደህንነት-ጥበቃ ድንጋጌ)ን ጨምሮ፤ የDCPSን መስፈቶችን ያስተላልፋል። ስለዚህ ፖሊሲ ያላችሁ ጥያቄዎች፣ ወደ 'Comprehensive Alternative Resolution and Equity (CARE) ቡድን፣ በdcps.care@k12.dc.gov መላክ ይችላል።

ይህ ፖሊሲ፣ ከዚህ ቀደም በዚህ በሚመለከተው ጉዳይ ላይ፣ በDCPS ታውጆ የነበረውን ሁሉንም ፖሊሲ፣ ሜሞራንዳ (memoranda)፣ እና መመሪያ የሚሰርዝ እና የሚተካ ነው።

## II. ሥልጣን እና በስራ ላይ የሚውል ሕግ[1]

| ምንጭ | ጥቅስ (Citation) |
|---|---|
| የፌደራል ሕግ | - አንቀጽ 9 (Title IX) የ1972 የትምህርት ማስተካከያ-የተደረገበት ድንጋጌ (Education Amendments Act)፣ (Title IX), 20 U.S.C. § 1681<br>- የ1973፣ ክፍል 504 መልሶ-ማቋቋም ድንጋጌ (Section 504 of the Rehabilitation Act of 1973)፣ 29 U.S.C. § 701 *et seq*.<br>- የአንቀጽ 2 (Title II)፣ የ1990 የአሜሪካውያን የጉዳተኝነት ድንጋጌ (Americans with Disabilities Act)፣ 42 U.S.C. § 12101 *et seq*.<br>- አንቀጽ 6 (Title VI)፣ የ1964 የሰብዓዊ መብቶች ድንጋጌ (Civil Rights Act)፣ 42 U.S.C. § 2000d *et seq*. |
| የፌደራል ደንቦች | - አንቀጽ 9 (Title IX) የማስፈጸሚያ ደንቦች (implementing regulations)፣ 34 C.F.R. Part 106 |
| የኮሎምቢያ ዲስትሪክት ሕግ | - የ1977 የዲሲ የሰብዓዊ መብቶች ድንጋጌ (DC Human Rights Act)፣ D.C. Code § 2-1401 *et seq*.<br>- የ2004፣ የዲሲ የቋንቋ እገዛ ማግኘት ድንጋጌ (Language Access Act of 2004) D.C. Code § 2-1931 *et seq*.<br>- የ2018፣ የትምህርት ቤት የደህንነት-ጥበቃ ኦምኒባስ (Omnibus) ማስተካከያ ድንጋጌ (School Safety Omnibus Amendment Act)፣ D.C. Code § 38-951 *et seq*. and D.C. Code § 38-952 *et seq*.<br>- እንዲደረግ-የታዘዘ የሪፖርተር መስፈርቶች (Mandated Reporter Requirements)፣ D.C. Code 4- *et seq*. |
| የኮሎምቢያ ዲስትሪክት የማዘጋጃ ቤት ደንቦች | - የተማሪ ቅሬታ ሂደቶች (Student Grievance Procedures)፣ 5-B DCMR § 2405<br>- ለወላጆች፣ አሳዳጊዎች፣ እና ጎብኚ-እንግዶች፤ ቅሬታ ሂደቶች (Grievance Procedures for Parents, Guardians, and Visitors)፣ 5-E DCMR § 405 |

[1] Nothing in this policy will supersede federal, state, or local law.

## III. ቁልፍ-የሆኑ አባባሎች እና ትርጉሞች

**መበሳጨት/ቅር-መሰኘት (Aggrieved)** ማለት፣ አንድ-ግለሰብ ወይም የግለሰቦች-ቡድን የሆኑ፤ በወሲባዊ ትንኮሳ (Sexual harassment)፣ ወሲባዊ ጥቃት (Sexual assault)፣ ወይም በፍቅር-ጓደኝነት ጊዜ (Dating) ጥቃትን አካትቶ - ተገቢ-ያልሆነ ተግባራት-ተሞክሮ ሲገጥማቸው፤ ማለት ነው።

**ስምምነት-መስጠት (Consent)** ማለት፣ በቃላቶች ወይም ግልጽ-በሆነ ድርጊቶች - ለቀረበው የወሲባዊ ክንውን ወይም ንክኪ ጥያቄ፣ በራስ-ነፃ ፍላጎት ስምምነት መስጠትን ማሳየት ማለት ነው። የቃላት ወይም የአካላዊ እንቢተኝነት ወይም የተቀባይነት-ሁኔታን - በመበሳጨት፣ ኃይልን-በመጠቀም፣ በማስፈራራት፣ ወይም በምላሽ-ሰጪው አስገዳኝነት ያለመኖሩ - ስምምነት እንደነበረ ሊያካትት አይችልም። (D.C. Code § 22- 3001(4))

**የፍቅር-ጓደኝነት (Dating partner) ወይም የጠበቀ ወዳጅነት (intimate partner)** ማለት፣ በመጀመሪያ-ላይ፣ በማህበራዊ-ግንኙነት ባለው የወሲብ፣ የፍቅር፣ ወይም የጠበቀ-ግንኙነት ባለው መልኩ፣ አልፎ-አልፎ (casual)፣ በጠበቀ-ሁኔታ (serious)፣ ወይም ለረጅም-ጊዜ፤ ተብሎ በሚመደብ ሁኔታ ማንኛውም ሰው፣ ከሌላው ሰው ጋር ያለው ግንኙነት (relationship) ማለት ነው። (D.C. Code § 38-952.01(1))

**በፍቅር-ጓደኝነት ጊዜ የሚደርስ ጥቃት (Dating violence)** ማለት፣ በፍቅር-ጓደኝነት ላይ ያለው ወዳጅ ላይ፣ ማስፈራራትን ሲጠቀም፣ ወይም በእውን ሲጠቀም፣ በአካላዊ፣ ስሜታዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ቴክኖሎጂያዊ፣ ወይም ወሲባዊ ጥቃትን ኃይልን-ለማሳየት ወይም በአሁኑ-ጊዜ ባለው ወይም ከዚህ-ቀደም በነበረው የፍቅረኝነት-ወዳጅነት ላይ የበላይ-ተቆጣጣሪ መሆንን ለማሳየት፤ የሚያንሳቁል ወይም አስገዳጅ የሆነ ባህሪይ ማለት ነው። (D.C. Code § 38-952.01)

**የቤት ውስጥ ጥቃት (Domestic violence)** ማለት፣ አካላዊ ጉዳትን የሚያስከትል፤ አካላዊ-ህመም ወይም ቁስለትን ጨምሮ፤ በእርግጠኝነት የቅርብ ከባድ የሆነ አካላዊ ጉዳት ወይም ሞትን ለማስከተል ወይም ለመፍጠር-አስቦ፣ በቤተሰብ ውስጥ ጥቃት ማድረስ ማለት ነው።

**ጠበኝነት-ፈጣሪ የሆነ አካባቢ (Hostile environment)** ማለት፤ ከትምህርት ቤት ፕሮግራሞች ወይም እንቅስቃሴዎች ከሚገኙ ጥቅማ-ጥቅሞች ወይም ባህሪይው ጉልህ-በሆነ ሁኔታ ከፍተኛነት ያለው፣ ተደጋጋሚ የሆነ፣ ወይም በተስፋፋ-ሁኔታ የሚከለክል ወይም የአንድ ሰው ሊኖረው ከሚችለውን አቅም በማገድ እንዳይካፈል የሚያደርግ አካባቢ ማለት ነው።

**ስምምነት ያልተደረበት (Non-consensual) የወሲብ ምስሎች (pornography)** ማለት፣ አንድ ወይም ከዚያ በላይ የሌላን ተለይቶ-የሚታወቅ ወይም ተለይቶ የማይታወቅን ሰው ወሲባዊ ምስሎችን፣ አውቆና ሆን-ብሎ የሚያሳይ ሰው ሲሆን፣ ይህም የሚሆነው:

- እንዲገለጽ የተደረገው ሰው፣ ወሲባዊ ምስሉ እንዲለቀቅ ስምምነት-ያልሰጠ፣
- እንዲገለጽ በተደረገው ሰው እና አሳልፎ በለቀቀው ሰው መካከል፣ የወሲብ ምስሉ ለሌላ እንደማይገለጽ - ስምምነት እና የመረዳት-ሁኔታዎች ከነበሩ፣ እና
- የወሲብ ምስሉን አሳልፎ እንዲገለጽ ያደረገው ሰው፣ ይህን ያደረገው ሆን-ብሎ ምስሉ ላይ ያለውን ሰው ለመጉዳት ወይም የገንዘብ ጥቅም ለማግኘት ከሆነ። (D.C. Code § 22-3052)

**የኲዊድ ፕሮ ኮ (Quid pro quo) ትንኮሳ** ማለት፤ እርዳታን፣ ጥቅማ-ጥቅምን ወይም አገልግሎትን - አንድን-ግለሰብ ከሚሳተፍበት አቅርቦት፤ ተቀባይነት-በሌለው የወሲባዊ ባህሪይ ካልተሳተፉ፣ እንዳያገኙ መከልከል ማለት ነው።

**የበቀል-እርምጃ (Retaliation)** ማለት፤ አንድ ሰው፣ ፆታዊ በሆነ መጥፎ-ባህሪይ ላይ ሪፖርት ባደረገው ነገር ምክንያት፤ ፆታዊ በሆነ መጥፎ-ባህሪይ መካፈልን ወይም የአድልዎ እንቅስቃሴን በመቃወሙ ወይም ምርመራ በማድረጉ፤ (ለምሳሌ፤ አቤቱታዎችን-ማቅረቢያ/petitionን በመፈረም) የተወሰደበት እርምጃ ማለት ነው።

**ወሲባዊ ጉዳት (ወይም ወሲባዊ ጥቃት)/Sexual assault (or sexual violence)** የሚባለው፤ ማንኛውም ከሚከተሉት ውስጥ ማለት ነው: የመጀመሪያ ደረጃ (first degree) የወሲብ ጉዳት (D.C. Code § 22-3002); ሁለተኛ ደረጃ (second degree) የወሲብ ጉዳት (D.C. Code § 22-3003); ሦስተኛ ደረጃ (third degree) የወሲብ ጉዳት (D.C. Code § 22-3004; አራተኛ ደረጃ (fourth degree) የወሲብ ጉዳት (D.C. Code § 22-3005); በደል-የሚያደርስ የወሲብ ጉዳት (misdemeanor sexual abuse) (D.C. Code § 22-3006); ወይም ወሲባዊ ጥቃቶችን ለመፈፀም ሙከራ ማድረግ (D.C. Code § 22-3018).

የመጀመሪያ ደረጃ (First degree) የወሲብ ጉዳት ማለት፤ በሁኔታው ውስጥ የተሳተፈው ሰው ወይም ሌላን ሰው እንዲሳተፍ ያደረገው ወይም በሚከተሉት ተግባራት ውስጥ በወሲባዊ ክንውኖች ለመሳተፍ የገባ:

- በሌላኛው ሰው ላይ ኃይልም በመጠቀም፣

- በማስፈራራት ወይም ያንን ሌላ ሰው ይሆናል-ተብሎ በሚታሰበው ፍርሃት ውስጥ በመክተት፣ ማንኛውንም ሰው ለሞት፣ ለአካላዊ ጉዳት ወይም ለማፈን (kidnapping) በሚዳርገው ሁኔታ ውስጥ ማስገባት፣
- ያ-ሌላ ሰው፣ ንቃተ-ህሊናውን እንዲስት ከተደረገ በኋላ፣ ወይም
- በኃይል በዚያ በሌላ-ሰው ላይ ከተፈጸመበት፣ ወይም ኃይልን ለመጠቀም ማስፈራራት ከተደረገ፣ ወይም ያ-ሌላ ሰው ሳያውቅ ወይም ፈቃደኛ ሳይሆን፣ በዕጽ፣ የሚያሰክሩ-ነገሮችን፣ ወይም ሌሎች ተመሳሳይ - በጉልህ-ሁኔታ የዚያን ሌላ ሰው አቅም የሚያግድ ወይም ባህሪውን የሚቆጣጠር አደንዛዥ ዕፅ እንዲደረግበት ከተደረገ በኋላ ሲፈጸም።

የሁለተኛ ደረጃ (Second degree) የወሲብ ጉዳት ማለት፤ በሁኔታው ውስጥ የተሳተፈው ሰው ወይም ሌላን ሰው እንዲሳተፍ ያደረገው ወይም በሚከተሉት ተግባራት ውስጥ በወሲባዊ ክንውኖች ለመሳተፍ የገባ:

- በማስፈራራት ወይም ያንን ሌላ ሰው ይሆናል-ተብሎ በሚታሰበው ፍርሃት ውስጥ በመክተት፣ (ማንኛውንም ሰው ለሞት፣ ለአካላዊ ጉዳት ወይም ለማፈን (kidnapping) በሚዳርገው ሁኔታ ውስጥ ከማስገባት-ሌላ የሆነ፣ ወይም
- በዚያ-ሌላ ሰው ላይ የሚከተሉት መሆናቸውን፤ ሰውየው የሚያውቅ ወይም የሚያውቅበት ምክንያት ካለው:
    - የባህሪው ምን ዓይነት አመጣጥ እንዳለው፣ መገምገም አለመቻል፣
    - በዚያ በወሲባዊ ድርጊት ውስጥ መካፈልን-እንቢ ለማለት የማይችል፣ ወይም
    - በዚያ በወሲባዊ ድርጊት ውስጥ መካፈልን አለመፈለግን በመነጋገር መግለጽ የማይችል ከሆነ።

ሦስተኛ ደረጃ (Third degree) የወሲብ ጉዳት ማለት፤ በሁኔታው ውስጥ የተሳተፈው ሰው ወይም የወሲባዊ ንክክ እንዲፈጠር ያደረገው ወይም በሌላ ሰው በሚከተሉት ተግባራት ውስጥ የተሳተፈ:

- በሌላኛው ሰው ላይ ኃይልም በመጠቀም፣
- በማስፈራራት ወይም ያንን ሌላ ሰው ይሆናል-ተብሎ በሚታሰበው ፍርሃት ውስጥ በመክተት፣ ማንኛውንም ሰው ለሞት፣ ለአካላዊ ጉዳት ወይም ለማፈን (kidnapping) በሚዳርገው ሁኔታ ውስጥ ማስገባት፣
- ያ-ሰው፣ ንቃተ-ህሊናውን እንዲስት ከተደረገ በኋላ፣ ወይም
- በኃይል በዚያ-ሰው ላይ ከተፈጸመበት፣ ወይም ኃይልን ለመጠቀም ማስፈራራት ከተደረገ፣ ወይም ያ-ሌላ ሰው ሳያውቅ ወይም ፈቃደኛ ሳይሆን፣ በዕጽ፣ የሚያሰክሩ-ነገሮችን፣ ወይም ተመሳሳይ - በጉልህ-ሁኔታ የዚያን ሌላ ሰው አቅም የሚያግድ ወይም ባህሪውን የሚቆጣጠር አደንዛዥ ዕፅ እንዲደረግበት ከተደረገ በኋላ ሲፈጸም።

አራተኛ ደረጃ (Fourth degree) የወሲብ ጉዳት ማለት፤ በሁኔታው ውስጥ የተሳተፈው ሰው ወይም የወሲባዊ ንክክ እንዲፈጠር ያደረገው ወይም በሌላ ሰው በሚከተሉት ተግባራት ውስጥ የተሳተፈ:

- በማስፈራራት ወይም ያንን ሌላ ሰው ይሆናል-ተብሎ በሚታሰበው ፍርሃት ውስጥ በመክተት፣ (ማንኛውንም ሰው ለሞት፣ ለአካላዊ ጉዳት ወይም ለማፈን (kidnapping) በሚዳርገው ሁኔታ ውስጥ ከማስገባት-ሌላ የሆነ፣ ወይም
- በዚያ-ሌላ ሰው ላይ የሚከተሉት መሆናቸውን፤ ሰውየው የሚያውቅ ወይም የሚያውቅበት ምክንያት ካለው:
    - የባህሪው ምን ዓይነት አመጣጥ እንዳለው፣ መገምገም አለመቻል፣
    - በዚያ በወሲባዊ ባህሪይ ውስጥ መካፈልን-እንቢ ለማለት የማይችል፣ ወይም
    - በዚያ በወሲባዊ ባህሪይ ውስጥ መካፈልን አለመፈለግን በመነጋገር መግለጽ የማይችል ከሆነ።

**ወሲባዊ ትንኮሳ (Sexual harassment)** ማለት፤ ማንኛውም ተቀባይነት ያላገኘ ወይም ያልተጋበዘ የወሲባዊ-እርምጃን በመውሰድ መጀመርን፣ ወሲባዊ የሆነ ውለታዎችን መጠየቅ፣ ወሲብን የሚያበረታታ አካላዊ እንቅስቃሴ ማድረግ፣ አድብቶ-መከታተል (stalking) ወይም ሌላ የቃላት ወይም አካላዊ የሆነ ወሲባዊ ምልከታ ያላቸውን ባህሪያትን በማሳየት፣ የሚከተሉትን ይሆናል-ተብሎ በሚገመት ሁኔታ ማድረግ:

- የተበሳጨውን-ሰው፣ ይሆናል-ተብሎ በሚገመት አስፈሪ የሆነ የአካላዊ ጉዳት በራሳቸው ላይ ወይም በንብረታቸው ላይ ማድረስ፣
- በተበሳጨው ላይ - አካላዊ ወይም አዕምሮአዊ ጤንነት ላይ፣ ጉልህ የሆነ የጉዳት-ውጤት የሚያደርስ ነገር መፍጠር፣
- በተበሳጨው ላይ የቀለም-ትምህርት ክንውን ላይ ወይም በትምህርት-ገበታ መገኘት (attendance) ላይ ጉልህ-በሆነ ሁኔታ መስተጓጎልን መፍጠር፣ ወይም
- በተበሳጨው-ሰው የመሳተፍ አቅሙ ላይ ወይም በአገልግሎቶች፣ እንቅስቃሴዎች ወይም አገልግሎቶች በሚያገኘውን ጥቅማ-ጥቅሞች ላይ ጉልህ-የሆነ መስተጓጎልን መፍጠር። (D.C. Code § 38-952.01(5))

***ፆታዊ የሆነ መጥፎ-ባህሪይ* (Sexual misconduct)** ማለት፤ ማንኛውም በቃላት፣ ቃላት-አልባ፣ በፅሁፍ፣ ወይም በኤሌክትሮኒክ ግንኙነት፣ ወይም በማንኛውም ሌላ ወደዚያ ሰው የተላከ ድርጊት ወይም የወሲብ ግንኙነትን፤ ወሲባዊ ግብዣን በመላክ፣ የመገናኛ-ቀን ወይም ቀኑን በማቀናበር (dating or soliciting a date)፣ በወሲባዊ የውይይት ምልልስ መሳፈፍ፣ ወሲባዊ ባህሪ ያላቸውን አስተያየቶች መስጠት፣ ከዚህ-ቀደም የነበሩ የወሲባዊ ተሞክሮዎችን ማስረዳት፣ ወይም ለወሲባዊ-ሁኔታዎች ወይም ወሲባዊ-አነሻሽነት ላላቸው ሁኔታዎች አካላዊ መጋለጥን ማድረግ ጨምሮ፤ ከተማሪው ጋር ለመፈጸም ከተመደበው ተማሪ ጋር ማድረግ ማለት ነው። (D.C. Code § 38-951.01(4))

***ለአቅመ-አዳም/ሄዋን ያልደረሱን በመጠቀም የወሲብ ጥቃት መፈጸም* (Sexual performance using minors)** ማለት፤ ይህም ወላጅን፣ ሕጋዊ አሳዳጊን፣ ወይም ለአቅመ-አዳም/ሄዋን ያልደረሱን (minor) ጥባቂን ሊያካትት ይችላል፤ ዕድሜው ከ18 ዓመት በታች የሆነን፤ ቅጥር፣ ሃላፊነት-የመስጠት፣ ወይም የሚያግባባ-ነገርን - በአንድ-ሰው በወሲባዊ ክንውን ውስጥ በማሳተፍ መጠቀም ማለት ነው። ይህ የሚያካትተው፣ አንድ ሰው የሚከተለውን ሲያደርግ:

- ከዚህ-ቀጥሎ ያለውን ባህሪና ይዘትን፣ ምርቶችን፣ መሪዎችን ማወቅ፣ ወይም እንዲደረግ-ማበረታታት፤ ዕድሜው ከ18 ዓመት በታች የሆነ ሰው - ማንኛውንም የወሲብ-ክንዋኔን ጨምሮ፤
- ከዚህ-ቀጥሎ ያለውን ባህሪና ይዘትን ማወቅ፤ ዕድሜው ለአቅመ-አዳም/ሄዋን ባልደረሰ (minor)፣ ለመሳተፍ፣ ለማስተላለፍ፣ ወይም የወሲብ ክንውንን በባለቤትነት መያዝ። (*see* D.C. Code § 22-3102)

***ሠራተኛ* (Staff)** ማለት፤ የትምህርት ቤት ተቀጣሪ-ሠራተኛ ወይም የበጎ-ፈቃድ ሠራተኛ (volunteer)፣ ትምህርት ቤቱ በኮንትራክት የሚሰራበት አካል ተቀጣሪ-ሠራተኛ፣ ወይም ትምህርት ቤቱ እንደ ወኪል ሆኖ ከትምህርት ቤቱ ጋር በትምህርት ቤቱ ውስጥ ወይም በትምህርት ቤቱ ስፖንሰር በተደረጉ እንቅስቃሴዎች ውስጥ የሚሰሩ፤ ከትምህርት-ቤቱ ጋር በአጋርነት የሚሰራ-አካል ተቀጣሪ-ሠራተኛ ወይም የበጎ-ፈቃድ ሠራተኛ (volunteer) ማለት ናቸው። (D.C. Code § 38-951.01(5))

***አድብቶ-መከታተል* (Stalking)** ማለት፤ ከአንድ የተወሰነ ሰው ላይ አተኩሮ የሚደረግ፣ በዚያ ሰው ላይ በደህንነታቸው ወይም በሌሎች ደህንነት ላይ ፍራቻን በተገቢው ሁኔታ በማሳደር፤ ወይም ጉልህ የሆነ የስሜታዊ ጭንቀትን በመፍጠት ማሰቃየት ባህሪያቶች ውስጥ መሳተፍ ማለት ነው። (see D.C. Code § 2-1401.02(29A) and § 22-3133)

***ደጋፊ የሆኑ እርምጃዎች* (Supportive measures)** ተማሪውን በመወከል - ከቅሬታ ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን ለመፍታት የሚወሰዱ እርምጃዎች ናቸው፤ (ለምሳሌ፤ የደህንነት-ጥበቃ ዕቅድን መፍጠር፣ የክፍል-ውስጥ የጊዜ-ሰሌዳን ማስተካከል፣ ማማከር)።

**የአንቀጽ 9 (Title IX) የ1972፣ የትምህርት ማስተካከያ ድንጋጌ of the Education Amendments Act of ("Title IX")** የሚያመለክተው፤ የፌደራል የሰው-ልጅ መብቶች ሕግ በያዘው፣ ማንም በአሜሪካ አገር (United States) የሚገኝ ሰው፣ በፆታ ላይ መሠረት ባደረገ - ከሚሳተፍበት መከልከል፣ ከጥቅማ-ጥቅሞች መከልከል፣ ወይም በማንኛውም የትምህርት ፕሮግራም ውስጥ ወይም ከፌደራል የገንዘብ እርዳታን ከሚያገኝ እንቅስቃሴ-በአድልዎ ተገዢ ሊደረግ አይችልም። የአንቀጽ 9 (Title IX) አድልዎ፤ የሚያካትተው - በፍቅር-ጓደኝነት ጊዜ (Dating) ጥቃት፣ የቤት ውስጥ ጥቃት (Domestic Violence)፣ የ'ድ ፕሮ ኮ (quid pro quo) ትንኮሳ፣ ወሲባዊ ጥቃት (Sexual assault)፣ አድብቶ-መከታተል (stalking)፣ እና ተቀባይነት የሌለው ባህሪይን ያካተተ ነው።

***ተቀባይነት የሌለው ባህሪይ* (Unwelcome conduct)** ማለት፤ ተቀባይነት የሌለው ባህሪይ (unwelcome conduct) ይሆናል-ተብሎ በተወሰነው ሰው - በጣም ከፍተኛ የሆነ፣ የተስፋፋ፣ እና በተጨባጭ አጸያፊ በሆነ ሁኔታ፤ የተቀባዩን በትምህርት ፕሮግራም እና እንቅስቃሴው ውስጥ፣ የአንድን-ሰው በፍትሃዊነት እኩል በሆነ መንገድ-የማግኘት በትክክል መከልከልን የሚወስን ነው።

## IV. መስፈርቶች

### A. *ሪፖርት ለማድረግ የሚከለከል እና መስፈርቶቹ*

DCPS፣ ተማሪ-በተማሪ ላይ የሚፈጥረውን ፆታዊ-የሆነ መጥፎ-ባህሪይን በጥብቅ ይከለክላል፤ ይኸውም የሚያካትተው፣ በፍቅር-ጓደኝነት ጊዜ (dating) ጥቃት፣ የቤት ውስጥ ጥቃት (Domestic Violence)፣ ስምምነት ያልተደረበት (Non-consensual) የወሲብ ምስሎች (pornography)፣ የ'ኲዊድ ፕሮ ኮ' (quid pro quo) ትኮሳ፣ የበቀል-እርምጃ፣ የወሱብ ጥቃት (Sexual assault)፣ የወሲብ ትንኮሳ (Sexual harassment)፣ ለአቅመ-አዳም/ሄዋን ያልደረሱን በመጠቀም የወሲብ ጥቃት መፈጸም፣ አድብቶ-መከታተል (stalking) እና ተቀባይነት የሌለው ባህሪይ አካትቶ ይሆናል። ማንኛውም የትምህርት ቤት ሠራተኛ አባል የሚያውቀው ወይም ሊያውቀው-የሚገባው ነገርን - እንደ ይህን-መሠል ድርጊት መከናወኑ፣ የተወነጀለውን ድርጊት ለ'DCPS CARE' ቡድን ሪፖርት ማድረግ ጨምሮ - ከዚያም-በመቀጠል፤ ትምህርት ቤቱ ወዲያውኑ የሚወስደው እና ተገቢ-የሆነ የምላሽ እርምጃ ነው።

በትምህርት ቤት ዝግጅቶች እና እንቅስቃሴዎች ወቅት፣ የቦታቸው ሁኔታ ምንም-ሆነ ምን፤ እና ወደ ትምህርት ቤት እና ከትምህርት ቤት የሚደረጉ ጉዞዎች፣ የትምህርት ቤት ዝግጅቶች፣ እና እንቅስቃሴዎች ጊዜ፤ ይህ በትምህርት ቤት ውስጥ በሚከሰቱ-ነገሮች እርምጃዎች ላይ በሚከናወን ጊዜ የሚካተት ነው። በማህበራዊ ሚዲያ ላይ የሚደረግ ግንኙነትን ሊያካትት የሚችል፣ ወይም ከትምህርት ቤት ንብረት ውጪ የሆነ ግንኙነትን፤ በተማሪው ደህንነት ወይም በትምህርት ቤት ውስጥ ያለው ከንውን ላይ ተጽዕኖ የሚያደርግ ነው። ከፆታዊ መጥፎ-ተግባር ጋር ግንኙነት ያለው በዚህ ፖሊሲ የሚከለክለው - ተጨማሪ ምሳሌዎች የሚያካትተው፤ ነገር ግን በዚህ ብቻ ያልተወሰነ:

- ወሲባዊነትን በትኩረት የሚገልጹ ምስሎችን፣ ፎተግራፎችን፣ ቪዲዮዎችን ወይም ማንኛውም ሌላ ሚዲያን፤ ከተቀባዩ እና በዚህ ውስጥ የተካተቱት ሁሉ ስምምነት መስጫ ሳይገኝ ማስተላለፍ፣
- አውቆና ሆን-ብሎ፣ ስምምነት ያልተደረበት (Non-consensual) የወሲብ ምስሎች (pornography) አሳልፎ-መስጠት፣ እና
- ለአቅመ-አዳም/ሄዋን ያልደረሱን በመጠቀም የወሲብ ጥቃትን መጠየቅ ወይም እንዲደረግ ማበረታታት።

ማንኛውም ተማሪ-በተማሪ ላይ የሚፈጥረው ፆታዊ-የሆነ መጥፎ-ባህሪይ የሆነ ክስ እንዳለ በሚታወቅ ጊዜ፣ ትምህርት ቤቱ ወዲያውኑ የሚወስደው - ነገሩን-የሚያቋርጥበት ወይም የሚያቆምበት እርምጃዎችን መውሰድ፣ እንዳይፈጠር መከላከል፣ እና የሚያስከትለውን ጉዳት መግለጽ አለበት።

ቅሬታውን ፋይል ካደረጉ በኋላ፣ ደጋፊ የሆኑ እርምጃዎች (supportive measures)፣ በዚህ-ውስጥ የተካተቱት ተማሪዎች በሚያስፈልጋቸው-ነገሮች ላይ መሠረት በማድረግ ይሰጣል። ደጋፊ የሆኑ እርምጃዎች (Supportive measures)፣ የሚያካትተው፤ ማንኛውም DCPS ተማሪውን ወክሎ ከቅሬታ ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን ለመፍታት የሚወሰዱ እርምጃዎች ናቸው፤ (ለምሳሌ፤ የደህንነት-ጥበቃ ዕቅድን መፍጠር፣ የክፍል-ውስጥ የጊዜ-ሰሌዳን ማስተካከል፣ ማማከር)። አስፈላጊ-ነው ተብሎ ከተወሰነ፣ የ'DCPS CARE' ቡድን፣ መፈጸሙን ለማረጋገጥ ከአካባቢው ትምህርት ቤቶች ጋር ይሠራሉ። ከዚህም በተጨማሪ፣ ሁሉም የDCPS ተቀጣሪ-ሠራተኞች፣ ይህን መሠል ክስተቶችን የተማሪው ባህሪይ የሚጠቁመው፣ እርሱ ወይም እርሷ የልጅ ወሲባዊ ጉዳት (Sexual abuse)፣ ወይም የልጅ-ጥቃት (Child Abuse) መድረሱን የሚያሳይ ከሆነ፤ ለልጅ እና ቤተሰብ አገልግሎት ኤጀንሲ (Child and Family Services Agency (CFSA) እና ለሜትሮፖሊታን የፖሊስ መምሪያ (Metropolitan Police Department (MPD)፣ ሪፖርት እንዲያደርጉ ስልጠና ይሰጣቸዋል። ጉዳት-የደረሰበት ተማሪ አቤቱታ ፋይል አደረገም አላደረገ፣ ወይም በሌላ-መልኩ ትምህርት ቤቱ እርምጃ እንዲወስድ ጠየቀም-አልጠየቀ፤ በዚህ ፖሊሲ ላይ የተዘረዘሩት ሂደቶች መጠናቀቅ አለባቸው።

### B. በተከለከሉ ባህሪያቶች ላይ የሚደረጉ ምርመራዎች እና የሚያስከትሉት-ውጤቶች

ተማሪ-በተማሪ ላይ የሚፈጥረው ፆታዊ-የሆነ መጥፎ-ባህሪይ ላይ ክስ የሚፈጥር አቤቱታዎች፣ በ'DCPS CARE' ቡድን አማካኝነት፣ እንደ በDCPS ውስጥ፣ የተማሪዎች እና በአጠቃላይ ሕዝቡ፣ ፋይል የተደረጉ ቅሬታዎች ላይ ምላሽ መስጠት ሂደቶች ዝርዝር መሠረት፤ ምርመራ የሚደረግበት እና ምላሽ-የሚስጥበት ይሆናል። የቅሬታ ምርመራ ፖሊሲው፣ የአቤቱታ አቅራቢዎችን ሚስጢራዊነትን መጠበቅን ጨምሮ፣ ምርመራ የተደረገበትን ሂደት ዝርዝሮች ይገልፃል።

ከዚያ ፖሊሲ ጋር የተያያዙትን እና ሁሉንም በአካባቢው እና በፌደራል ህግ እና ደንቦች ላይ በስራ-ላይ በሚውሉ ነገሮች ላይ፤ የእርማት እርምጃዎቹ ይከናወናሉ። የ'DCPS CARE' ቡድን፤ ጉዳትን መጠገንን እና ተለይቶ የታወቀውን ማንኛውም ስልታዊ ውድቀትን ለማረም የሚጠይቅ ሲሆን፤ ይህም ሊያካትት የሚችለው - የፖሊሲ ለውጥ፣ ለተማሪዎች የሚሰጡ የአገልግሎት ስምምነቶች፣ እና/ወይም በምላሽ-ሰጪ ላይ የሚደርስ የስነምግባር እርምጃን ጨምሮ ይሆናል። የስነምግባር እርምጃው የሚከናወነው፣ በ'DCPS *K-12 Discipline Policy*' ጋር በተገናኘ፣ እንደ ተማሪ-በተማሪ ላይ የሚፈጥረውን ፆታዊ የሆነ መጥፎ-ባህሪይ[2] ያሉትን በመሠለ ሁኔታ ነው።

በተጨማሪም፤ አቤቱታዎቹ - በአንቀጽ 9 (Title IX) ስር ሊገቡ ይችሉ ይሆናል። የአንቀጽ 9 (Title IX) ቅሬታዎች፣ በአሁኑ በ'DCPS grievance policies'[3] ውስጥ የተዘረዘሩትን የምርመራ ሂደቶችን ይከተላል። ስለ አንቀጽ 9 (Title IX) ተጨማሪ መረጃዎችን ለማግኘት፣ የ'*Anti-Discrimination Policy': ተማሪዎች*[4] ተመልከቱ።

ምርመራዎቹን የሚያካሂደው የDCPS ሠራተኛ የሆነ፣ ተማሪ-በተማሪ ላይ የሚፈጥረውን ፆታዊ የሆነ መጥፎ-ባህሪይ ጋር ግንኙነት ያላቸው ጉዳዮች ላይ እና የአቤቱታ-አቅራቢዎችን ደህንነት የሚጠብቅ እና ተጠያቂነትን የሚያበረታታ የምርመራ-ሂደቶችን እንዴት ማድረግ እንደሚቻል፤ ዓመታዊ ስልጠናን ያገኛሉ ወይም ይካፈላሉ።

---

[2] *Available at* https://dcps.dc.gov/page/dcps-policies.

[3] *Available at* https://dcps.dc.gov/page/dcps-policies.

[4] *Available at* https://dcps.dc.gov/page/dcps-policies.

### C. የሕዝብ ግንዛቤ-ማሳደር እና መከላከል

ቢያንስ በአንድ የትምህርት ዓመት አንድ-ጊዜ፣ አቤቱታዎች የት ፋይል-ሊደረጉ እንደሚችሉ በዚህ ፖሊሲ እና መረጃ ላይ፤ ለተማሪዎች፣ ቤተሰቦች፣ እና የትምህርት ቤት ሠራተኞችን ትምህርት ቤቶች ይሠጣሉ። ተማሪዎች እና ቤተሰቦች በአጥጋቢ-ሁኔታ ስለ ፖሊሲ እና ድንጋጌዎቹ መረዳታቸውን ለማረጋገጥ እንዲረዳው፤ ትምህርት ቤቶች ይህም ፖሊሲ በሚከተሉት ቦታዎች ውስጥ ይገኛሉ: በትምህርት ቤቱ ድህረ-ገጽ፣ በዋናው ቢሮ፣ በትምህርት ቤት ጤና ክፍል፣ በትምህርት ቤት ካውንስለር እና የትምህርት ቤት ማህበራዊ ሠራተኛ (Social Worker) ቢሮ፣ እና በወላጅ እና ተማሪ የመመሪያ መጽሐፍቶች[5] ውስጥ ይገኛሉ። ትምህርት ቤቶች ስለዚህ ፖሊሲ፤ በእድገታዊ-ሁኔታዎችን ተገቢነትን በጠበቀ ሁኔታ፣ ለተማሪዎች ያሳውቃሉ። ትምህርት ቤቶች፤ የጤና ካሪኩላ (health curricula)ን፣ ከወሲባዊ ትንኪሳ፣ የወሲብ ጥቃት፣ እና በፍቅር-ጓደኝነት ጊዜ (Dating) ጥቃት ጋር ተያያዥ በሆነ ነገር ላይ - እንደ የመነጋገሪያ መንገድን ከፋች-ሆኖ ለመጠቀም ያበረታታሉ።

በትምህርት ቤታችን ውስጥ፣ የመከላከልን እና በንቃት-ሆኖ የተማሪ-በተማሪ ላይ የሚፈጥረውን ፆታዊ የሆነ መጥፎ-ባህሪይ ላይ የሚደረጉ ነገሮች ላይ መፍትሄ በመስጠት፤ አስፈላጊነት ያለውን-ቦታ በመስጠት፣ DCPS የሚከተሉትን ያደርጋል:

- ሁሉም ተማሪዎች፣ የመወደድ ስሜት፣ ፈተናን ተቋቋሚነት፣ እና የዝግጁነት ስሜት የሚሰማቸውን አካባቢ መፍጠር፣
- ማህበራዊ-ስሜታዊነት የሙያ-ማሳደጊያ (professional development)ን ለDCPS ሠራተኞች መስጠት፣
- በባህላዊ ምላሽ መስጠት ትምህርት እና ልምምዶች ዙሪያ የሙያ-ማሳደጊያ (professional development)ን ለDCPS ሠራተኞች መስጠት፣
- በትምህርት ቤቶች ውስጥ እና በሌሎች የDCPS ቦታዎች ውስጥ፣ ፀረ-መድልዎ እና ትንኮሳ (harassment) ፕሮግራሞችን እና እንቅስቃሴዎችን ማካተት፣
- ተማሪ-በተማሪ ላይ የሚፈጥረውን ፆታዊ የሆነ መጥፎ-ባህሪይ ላይ የሚታዩትን የማስጠንቀቂያ ምልክቶች ለመለየት እንዲችሉ ለወላጆች መረጃዎችን ይሠጣል፤ እንዲሁም በስራ-ላይ የሚውሉ፣ የዕድሜ-ጋር የሚሄዱ - እነዚን መሠል ርዕሶችን ከተማሪዎች ጋር ለመወያየት መንገዶችን ይሠጣል፤
- ተማሪዎችን፣ እንክብካቤ-ሰጪዎችን፣ እና የትምህርት ቤት ጎብኚ-እንግዶችን፣ መድልዎ እና ትንኮሳ (harassment)ን ሪፖርት እንዲያደርጉ ማበረታታት፣
- የትምህርት ቤት ሠራተኞች፣ መድልዎ እና ትንኮሳ (harassment)ን ሪፖርት እንዲያደርጉ አስፈላጊ-ማድረግ፣
- የተደረገበት ምክንያት ምንም-ሆነ ምን፣ በክስተቱ-ላይ ምላሽ-ለመስጠት፤ ዲስትሪክት-አቀፍ ፕሮቶኮልን ማስፈጸም፣ እና
- መድልዎ የሚከናወንበር አካባቢዎ ካሉ ለመወሰን እና እንደ-የተገቢነቱ ምላሽ ለመስጠት፤ የአካባቢውን ሁኔታ ግምገማ ማድረጊያዎችን ማከናወን።

### D. የመረጃ-ምንጮች (Resources)፤ ተጽዕኖ ለደረሰባቸው ተማሪዎች እና ቤተሰቦች

የDC Victim Hotline፣ በስልክ፣ በቴክስት (text) ወይም በኦንላይን መጨዋወቻ (chat)[6] አማካኝነት 24/7 የሚገኝ ነው። ከከንቲባው ቢሮ የተጎጂ አገልግሎት እና ፍትህ የገንዘብ እርዳታ (Mayor's Office of Victim Services and Justice Grants (OVSJG) እና ለወንጀል ተጎጂዎች ብሄራዊ ማዕከል (National Center for Victims of Crime) ጋር በተደረገ አጋርነት አማካኝነት፣ የአጣዳፊ መስመሩ (hotline)- በኮሎምቢያ ዲስትሪክት ውስጥ፣ ሁሉን-አቀፍ መረጃ፣ የመረጃ ምንጮች፣ እና መምራቶችን ይሠጣል። የዲሲ ተጎጂ አጣዳፊ-መስመር (DC Victim Hotline)፣ በዲስትሪክቱ ውስጥ ያሉ እና፤ የአገልግሎት ሰጪዎችን ትብብር በመወከል የሚሰሩ፤ ከወንጀል ተጎጂ ጋር ችግር-የለሽ የሆነ ግንኙነት በማድረግ፣ ወደ ነፃ የመረጃ ምንጮች የሚመሩ እና፣ አካላዊ፣ የገንዘብ፣ ሕጋዊ፣ እና ስሜታዊ የወንጀል መዘዞችን በመዳሰስ ላይ፣ ለመርዳት ይሠራሉ። የአጣዳፊ-መስመሩን (Hotline)ን ለማነጋገር፣ በ1-844-4HELPDC (1-844-443-5732) ደውሉ ወይም ቴክስት (text) አድርጉ፤ ወይም የኦንላይን የመጨዋወቻ (cha)ን በ www.DCvictim.org/Chat አግኙ።

ተማሪ-በተማሪ ላይ የሚፈጥረውን ፆታዊ የሆነ መጥፎ-ባህሪይ ሳቢያ ለተጎዱ ተማሪዎች እና ቤተሰቦች የውጪ-የመረጃ ምንጮችን፣ አገልግሎቶችን፣ እና መረጃዎች፤ እባካችሁን የሚከተለውን ዝርዝሮች አማክሩ።

- Department of Behavioral Health's (DBH) Behavioral Resource Directory;
- MPD's Sexual Assault Resources List;

---

[5] Adapted from: US Department of Education Office for Civil Rights (January 2001). *Revised Sexual Harassment Guidance: Harassment of Students by Schools Employees, Other Students, or Third Parties: Title IX*, 20. Retrieved from: https://www2.ed.gov/about/offices/list/ocr/docs/shguide.pdf.

[6] DC Victim Hotline: https://ovsjg.dc.gov/page/dc-victim-hotline-now-available.

- MPD's Victim Specialists Unit; እና
- Office of the State Superintendent of Education (OSSE)'s Supporting Mental Health in Schools Resources List.[7]

## V. ፖሊሲውን ለማስፈጸም የሚፈለጉ መስፈርቶች

'DCPS'፣ ስለ መድልዎ የሚሰጡ አቤቱታዎች ላይ እርዳታ እና ምላሽ ለመስጠት የሚገኝ ይሆናል። እያንዳንዱ ትምህርት ቤት፤ አድሎአዊ አሰራር የደረሰባቸውን ተማሪዎች ለመርዳት፣ የማህበራዊ ሠራተኛ (social worker) እና/ወይም የአዕምሮ ጤና ቡድን ያሉት እና የማህበራዊ የመረጃ-ምንጮችን (resources) - የአማካሪ ድርጅቶች (advocacy organizations) እና ማህበረሰብ-ላይ መሠረት ያደረጉ አገልግሎቶችን ጨምሮ፣ በመለየት ይረዳሉ። የፍህታዊ-እኩልነት ስልት እና የፕሮግራም አሰራር ቡድን ደግሞ፣ የዕድሎች ክፍተቶችን በማጥፋት፣ ተቋማዊ-የተዛባ አመለካከትን የሚያስቆም እና በቀለም ትምህርት እና በማህበራዊ ስኬቶች ላይ እንቅፋቶችን የሚያስወግድ አካባቢን ለመፍጠት ይሰራል። የአድልዎ ሁኔታዎችን ተከትሎ፣ የቀለም-ትምህርት እርዳታ የሚገኝም ይሆናል።

DCPS እያንዳንዱን ተማሪ፤ በፍህታዊነት፣ የላቀ-በላጭነት፣ ግልጽነት፣ እና ተጠያቂነት ባለው-ሁኔታ ለማገልገል ቁርጠኝነቱን የሚያሳይ እና ለተማሪዎች የአድልዎ እና ከጥቃት ነፃ የሆነ አካባቢን መፍጠር ነው። ሁሉም የDCPS ተቀጣሪ-ሠራተኞች፤ በዚህ በተቀረጸው ፖሊሲ መስፈርቶች መገዛት ያስፈልጋቸዋል። የዚህ ፖሊሲ የማስፈጸም ህግ የሚጠበቀው፤ በመድልዎ (discrimination)፣ የአንቀጽ 9 (Title IX)፣ እና እንዲወስዱ-የሚያስገድደውን የሪፖርተር ስልጠናዎች[8]፤ ለሠራተኛ የተሰጠው እንዲሁም በቀጣይነት ቁጥጥር እየተደረገበት በ'DCPS Care' ቡድን በሚታየው ይሆናል። ይህን ፖሊሲ ላይ እና በአፈጻጸሙ በተመለከተ ጥያቄዎች ወይም ስጋቶች ካሉ፣ ወደ 'DCPS CARE' ቡድን፤ በdcps.care@k12.dc.gov ሊላኩ ይገባል። ስለ ተጨማሪ ስጋቶች ወይም በዚህ ትዕዛዛት ላይ ጥሰቶችን ለማሳወቅ፤ ይህን ትዕዛዝ መስጫ፣ የሃቀኝነት ሹሙ ዋና የሆነው (Chief Integrity Officer)ን ለማነጋገር፤ የኦንላይን-መምሪያ (Online Referral) ቅጽን[9] በመሙላት ወይም ወደ dcps.cio@k12.dc.gov ኢሜል መላክ።

የእንባ-ጠባቂ ቢሮ (The Office of the Ombudsman)፤ በቅሬታዎች ውስጥ ለተካተቱ ተማሪዎች፣ እንደ አማካሪ ሆኖ ሊያገለግል ይችል ይሆናል። ለተጨማሪ መረጃ፣ https://sboe.dc.gov/page/office-of-the-ombudsman-for-public-education ተመልከቱ ወይም የሚከተለውን ያነጋግሩ:

የስቴት የትምህርት ቦርድ (State Board of Education)
Office of the Ombudsman for Public Education
One Judiciary Square
441 4th Street, NW, 530S
Washington, DC 20001
ስልክ: (202) 741-0886
በeducation.ombudsman@dc.gov ኢሜል ያድርጉ።

[7] Please note, this is not an exhaustive list. Additional resources may be available.
[8] Trainings will be provided at time of hiring and, at minimum, every two years thereafter.
[9] *Available at* https://dcps.dc.gov/page/office-integrity.